የባልደራስ ድጋፍ በሰሜን አሜሪካ
Balderas Support in North America
www.balderasfordemocracy.com

ቀን፡ 15/08/2013

# ሀገርን የማዳን ጥሪ - የመጨረሻው መጀመሪያ

ለብዙ ሺህ አመታት በአባቶቻችን መስዋዕትነት የቆየችው ሀገራችን

ዐይናችን እያየ እጃችን ላይ ሳትፈርስ ሁላችንም በአንድ ላይ ልንቆም ይገባል!

የተከበራችሁ በሀገር ውስጥ እና ከሀገር ውጪ የምትኖሩ ኢትዮጵያዊያን፣

እኛ ኢትዮጵያዊያን የዛሬ ሦስት ዓመት በአገራችን የተካሄደው ለውጥ በልባችን ውስጥ ሰንቆት የነበረው ተስፋ ከህሊናችን በቀላሉ የሚጠፋ አይደለም። እንዲህ እንደዛሬው ተስፋችን የህልም እንጀራ ሆኖ መቅረቱ እውን ሳይሆን፤ ያንን ታላቅ ተስፋ በተለያየ ጎራ የነበርን ሁሉ ለሀገራችን ካለን ቀናኢ ምኞት እና ጉጉት የተነሳ በአንድነት "ሆ!" ብለን ተቋድሰናል። የተሰጠን ተስፋ መሬት ላይ ወርዶ ፍሬውን እናይ ዘንድም እንደየአቅማችን ደክመናል።

በእርግጥ ብዙዎች ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ባዶ ቃል ጋር በፍቅር ወድቀው የጫጉላ ሽርሽር ላይ በሚምነሸነሹበት በለውጡ መጀመሪያ ወቅት ሁሉም በተቀደደለት ቦይ ፈስሶ ነበር ማለች አይቻልም። ይልቁንም ነገሮችን አካሄድ በጥንቃቄ መርምረው የኦሮሙማውን መንግሥት የቃልና የተግባር ግጭት ነቅሶ በማጋለጥ በለጋነቱ እንዲታረም ያካልሆነ ግን ታላቅ አገራዊ ጥፋት እንደሚከተል በማለዳ የማንቂያ ደውል የደወሉ ብልሆች አልጠፉም። ለዚህም የባልደራስ ለእውነተኛ ዴሞክራሲ ፓርቲ ፕሬዚዳንት፣ አቶ እስክንድር ነጋ ግምባር-ቀደም ተጠቃሽ ናቸው። ደውሉን ሰምተን ተገቢውን ምላሽ የሰጠን በእውኑ ስንቶቻችን ነን? ያ ገና በማለዳ ችግሩ ሥር ሳይሰድ የተሰጠን ወርቃማ ዕድል እንደ ዋዛ አምልጦናል። ከዚያም በኋላ በተለያየ ጊዜ ለውጡ አቅጣጫውን መሳቱን ያመላከቱ ግለሰቦች እና ድርጅቶች ቢኖሩም ጆሮ ሳይሰጣቸው ታልፈዋል። በግለሰብ ስብዕና ግንባታ እና በባዶ የተስፋ ቃል ላይ ስናተኩር ሀገራዊ ህልውናን ችላ አልነው። ግለሰቦች እና ድርጅቶች ይመጣሉ፣ ይተካሉ። ሀገራችን ግን ከእኛ በፊት ነበረች፤ ከእኛም በኋላ ትቀጥላለች፤ መተኪያም የላትም።

አንኳር የሆኑ እና የሚያመሳስሉንን ጉዳዮች ትተን ጊዜያዊ በሆኑ በጥቃቅን ልዩነቶቻችን ላይ ስንመሰጥ የህወሀት/ኢህአዴግ የበኩር ልጅ የሆነው ኦህዴድ/ብልጽግና በሁሉም የሀገሪቱ ክፍሎች የጥፋት መዋቅሩን በመዘርጋት መጠነ-ሰፊ የዘር ጭፍጨፋውን በነፃነት እንዲያካሄድ መንገዱን አመቻችንለት።

አሁን ከአንድ መራር እውነት ጋር መጋፈጥ ግድ ብሎናል። ያ ከዛሬ ሦስት ዓመት በፊት የተሰጠን የተስፋ ስንቅ መክኖ በታላቅ ሀገራዊ ውርደት፣ ሀዘን እና ተስፋ መቁረጥ ተተክቷል። ዛሬ የኢትዮጵያ ህዝብ ትልቁ ጥያቄ ብልጽግና ሳይሆን ህልውና ነው። እድገት ሳይሆን ሰላም፣ መረጋገት እና ደህንነት ነው።

E-mail:balderasnorthamerica@gmail.com Tel: 240-838-1745 P.O. Box 43829

ሙሉ ሥልጣን ያለው መንግሥት ባለባት ሀገር ዜጎች ለደህንነታቸው ዋስትና የላቸውም። ለመንግሥት የሚከፍሉት ግብርም እነርሱኑ መልሰው ለማጥቃት ለሚውሉ ውድ ውድ የጦር መሣሪያዎች ግዥ እና ለአራጆቻቸው ቀለብ ይውላል። የኢትዮጵያ ህዝብ እንደሌሎች ህዝቦች ነገን በጉጉት ሳይሆን ከል ለብሶና በፍርሀት ቆፈን ተጠፍንጎ የሚጠብቅ አሳዛኝ ህዝብ ሆንዋል።

ወደድንም ጠላንም ኢትዮጵያ ዛሬ ልጆቿ የሚወለዱባት፣ የሚያድጉባት፣ ፍሬ የሚያፈሩባት፣ በክብር ተጦረው የሚቀበሩባት አይደለችም። ይልቁንም ጽንስ በግፍ የሚጨናገፍባት፣ ነፍስ ያላወቁ ህፃናት እንደ ፋሲካ ዶሮ የሚታረዱባት፣ ወጣቶች እየታደኑ የሚገደሉባት፣ እናቶች እና ሴቶች ልጆች እንዲሁም አስታራቂ ከዚያም አልፎ የትውልድ ኢንሳይክሎፒዲያ የሆኑ አረጋዊያን ከሰው ልጅ አእምሮ በላይ በሆነ አሰቃቂ ሁኔታ በግፍ ተሰቃይተው የሚገደሉባት፣ በክብር አፈር ለመቅመስ ያልታደሉባት፣ የብዙ ዜጎች ደብዛ የሚጠፋባት፣ የአራጅ ነፍሰ-በላዎች መተራመሻ አኬል-ዳማ ናት።

የሰው እምባ እንደውኃ አየፈሰሰ ነው። የሰው ደም እንደጎርፍ እየወረደ ነው። የጥሮ-ግሮ አዳሪው ሀብት እንደ ደመራ እየነደደ ነው። ቤተ-እምነቶች እና ቅርሳቅርስ እየወደሙ ነው። ህዝቡ ነፍሱን ከአራጆቹ ለማዳን ተወልዶ ያደገበትን ቀዬ ትቶ እግሩ ወዳመጣለት እየሸሸ ነው። የሰው ልጅ በግፍ ተፈናቅሎ በየሜዳው ተበትኗል። እናም ይህንን የመከነ ተስፋ ለልጆቻችን ለማስረከብ እየተንደረደርን እንገኛለን። ከዚህ በላይ አንገት የሚያስደፋ ነገር የለም።

ይህ ሁሉ ሲሆን ያሻግሩናል የተባሉት የሀገሪቱ ጠቅላይ ሚኒስትርም ሆኑ በየእርከኑ ያሉ አጋፋሪዎቻቸው ድርጊቱን ከኮሽታ አልቆጠሩትም። ይልቁንም የማቴሪያሊስትነት ዝንባሌያቸው ገሀድ እየወጣ የመጣው ጠቅላይ ሚኒስትር የሰው ህይወት መጥፋት ግድም ሳይሰጣቸው በመደበኛነት እየተፈጸመ ያለውን ሀገራዊ እልቂት ምንም እንዳልተፈጠረ ችላ ሲሉ ከመታዘብ አልፈን አፍረናል፣ አዝነናል፣ ተቆጭተናል። ለጊዜያዊ ብልጭልጭታ እና ቁሳቁስ ነገሮች ሰፊ ጊዜና ትኩረተቻውን ሲሰጡ ያለባቸው መንግሥታዊ ኃላፊነት ምንድን ነበር ብለን ግራ በመጋባት እንድንጠይቅ ተገድደናል።

አንዳንድ የዋሆች እንደሚሉት እየተደረገ ያለው ፍጅት ከጠቅላይ ሚኒስትሩ እና ፓርቲያቸው ዕውቅና ውጭ እንዳልሆነ አሁን ላይ ለሁሉም ግልፅ ሆኗል። "ከፈረሱ አፍ" እንደሚባለው ከእልቂቱ መሀል ለወሬ ነጋሪ የተረፉት ወገኖቻችን በተለያየ ጊዜ አስረግጠው እንደሚናገሩት በሀገራችን ህዝብ ላይ የተከፈተው የጥፋት ዘመቻ በአሳፋሪ ሁኔታ በመንግሥት መዋቅር የሚታገዝ ነው። የመንግሥቱን ሥልጣን የያዘው የብልጽግና ፓርቲ ሲሆን፤ የብልፅግና ፓርቲ ቁንጮ ደግሞ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ናቸው።

ሀገር እንዲመሩ ኃላፊነት የተሰጣቸው ባለሥልጣን ሀገር ሲጠፋ ካልተጠየቁ ማን ሊጠየቅ ይችላል? እኚህ ግለሰብ ህዝቡ ማንነታቸውን ሳይሆን ቃላቸውን አምኖ የሰጣቸውን አደራ በልተው በማንነቱ እያስጨረሱት ይገኛሉ። በህዝቡ ሀዘንና መከራ ላይ በፈገግታ ታጅበው ህንፃ፣ መናፈሻና ልዩ ልዩ አልባሳትን በማስመረቅ ከባህልም ከሰብአዊነትም ውጪ በሆነ ሁኔታ በህዝባችን ሀዘን እና መከራ ላይ ተሳልቀዋል።

ይህ ማስተባበያ የማይሻ እውነታ እኛ ስለፈለግነው ወይም ስላልፈለግነው የሚቀየር አይደለም። ችላ ብንለውም ለታሪክ ተሰንዶ የተቀመጠ ነውና ሀቀኛና ለሀገር ተቆርቋሪ ትውልድ ሲመጣ ይፋረዳቸዋል። በዚህ ዝምታችን ከቀጠልን የዛኔ እኛም ከተወቃሽነት አናመልጥም።

ለመሆኑ ይህ እልቂት ስንት ነፍስ እስኪቀር ድረስ ነው የሚቀጥለው? የእኛስ ዝምታ?

የመፍትሄ ሀሳባችንን እነሆ እንላለን!

### 1. የአፍዝ አደንግዝ ዘመን ይብቃ

ላፍታ ቆም ብለን ይኽንን ላለፉት ሦስት ዓመታት ያለማቋረጥ በዛች ምድር ላይ የተፈፀመን ግፍ በዘር፣ በኃይማኖት ወይም በፖለቲካ ፓርቲ ዐይን ሳይሆን በሰብአዊነት ዐይን ብቻ እንየው። ምን እየተካሄደ ነው? የጀመርነው መንገድስ ወዴት እየወሰደን ነው? ስንት ነፍስ ሲቀር ነው አቅጣጫ ለማስተካከል ወይም ለመቀየር የምናስበው? እየገባንበት ያለው የጥፋት አረንቋ ጥልቅ ነውና ከዚህ በላይ አንዘናጋ። ለህሊናችንም፤ ለታሪካችንም፤ በክብር አስረክቦን ላለፈው፣ ለአሁኑም ሆነ ለመጪው ትውልድ ስንል አንድ ጊዜ ልዩነታችንን ወደ ጎን አድርገን በጋራ እንቁም። የመከፋፈልን/የመለያየትን አስከፊነት አይተነዋልና አሁን ደግሞ ለአንድነት/ለህብረት ዕድል እንስጠው። ይኽንን ሀገራችንን የማዳን የመጨረሻው መጀመሪያ ዕድል አናምክነው። አሁንም በዘረ-መላችን የብልሆቹ፣ የአስተዋዮቹ፣ የጀግኖቹ እና የቆራጦቹ አያት፣ ቅድመ-አያቶቻችን፣ አባትና እናቶቻችን ጠብታ እንዳለ አንዘንጋ።

### 2. ኢትዮጵያዊ ኢትዮጵያዊነቱን ነብር ዥንጉርጉርነቱን አይለቅም

የሁላችን ዞሮ መግቢያ የሆነችው የጋራ ቤታችን ዐይናችን እያየ እጃችን ላይ እየፈረሰች ነው። ብዙ ልዩነቶች ቢኖሩንም ቢያንስ አንድ ሚዛን የሚደፋ የጋራ ነገር እንዳለን ማናችንም አንክደውም። ይኸውም ማንነታችን - ኢትዮጵያዊነታችን ነው። በሀገር ላይ የመጣን ወራሪ በጋራ ስንመክት ለመኖራችን ታሪክ ምስክር ነው። "ኢትዮጵያዊ ኢትዮጵያዊነቱን ነብር ዥንጉርጉርነቱን አይለቅም" እንደተባለው ዛሬም ሁሉም ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ ወደ አንድ መጥቶ ፋሽስታዊውን የኦሮሙማ አካሄድ በጋራ እንዲታገል ጥሪ እናቀርባለን።

### 3. እራስን መከላከል አማራጭ የሌለው ተግባር ነው

በግልጽ እንደምናየው ችግሩ እንደ ሰደድ-እሳት እየተቀጣጠለ የሁሉንም ቤት በፍጥነት እያንኳኳ ነው። ነገሮች በቶሎ መፍትሄ ካልተበጀላቸው በየትኛውም ክልል የሚገኝ የሀገራችን ህዝብ የዚህ መከራ ተቋዳሽ መሆኑ የጊዜ ጉዳይ ብቻ ነው። አለመታደል ሆኖ ዛሬ የኢትዮጵያ ህዝብ ይጠብቀኛል ብሎ የሚተማመንበት መንግሥት የለውምና ህብረተሰቡ እርስ-በእርሱ በመመካከር፣ በመደራጀት፣ በንቃት አካባቢውን በመቃኘት እና መረጃ በመለዋወጥ እራሱን ይጠብቅ። የሚመጣበትንም መንግሥት-መራሽ ወራሪ ኃይል በአልሞት ባይ ተጋዳይነት በጋራ ይመክት።

## 4. ምርጫ መራጭ ሲኖር ነው

በእውነቱ በዚህ ሰዓት ምርጫ ለኢትዮጵያ ህዝብ ችግር መፍትሄ ይሆናል? የማያጠግብ እንጀራ ከምጣዱ ያስታውቃልና ገና ከጅምሩ የኦህዴድ/ብልጽግና መንግሥት ቀንደኛ ተፎካካሪዎቼ የሚላቸውን መርጦ ያለወንጀላቸው በመወንጀል ያለምንም የፍርድ ውሣኔ በእስር እያንገላታቸው ይገኛል።

የባልደራስ ፓርቲ ፕሬዚዳንት አቶ እስክንድር ነጋ እና ባልደረቦቻቸው አቶ ስንታየሁ ቸኮል፣ ወ/ሮ አስቴር ስዩም እና ወ/ሪት አስካል ደምል የዚህ አሻጥር ሰለባ መሆናቸውን ህሊናችንን ለሆዳችን ካልሸጥን በስተቀር የማንክደው ሀቅ ነው። ፍትህ ወዴት አለሽ!?

ቀደም ብለን እንደገለጽነው አቶ እስክንድር ተከታዩ የጽልመት ዘመን ቀድሞ የሸተታቸው እና በታላቅ የሀገር ተቆርቋሪነት ስሜት ለህይወታቸውም ሳይሰሱ አደባባይ ወጥተው የኢትዮጵያንም ሆነ የቀሪውን ዓለም ህዝብ ስለጉዳዩ በማሳሰብ ሀገራዊ ግዴታቸውን የተወጡ ውድ የኢትዮጵያ ልጅ ናቸው።

የተፎካካሪ ፓርቲዎች በአንዳንድ ክልሎች ውስጥ በምርጫው መሳተፍ አለመቻል፣ የዕጩ ተወዳዳሪዎች በአሳዛኝ ሁኔታ በግፍ መገደል፣ አንዳንድ ተፎካካሪ ፓርቲዎች በመገናኛ ብዙሀን ቀርበው በምርጫ ክርክር ላይ በመሣተፍ ሀሳባቸውን ለመራጩ ህዝብ እንዳይሸጡ ዕድል መነፈግ፣ እና የምርጫ ካርድ ተለይተው ለተዘጋጁ መራጮች ብቻ በተናጠልና በምስጢር መታደል እና የመሳሰሉ ችግሮች ገሀድ መውጣታቸው የምርጫውን ፍትሀዊነት ከወዲሁ ጥያቄ ውስጥ ከትቶታል።

አብዛኛው የህብረተሰብ ክፍል የምርጫ ካርድ ለመውሰድ እምቢተኝነት ማሳየቱም አስቀድሞ በምርጫው ውጤት ተስፋ ለመቁረጡ አረጋጋጭ ነው። ከዚያም አልፎ ሀገሪቷ በከፍተኛ የተቃውሞ ማዕበል መናወጥ ጀምራለች።

ከሁሉም በላይ ግን ህዝባችን በሀዘን ልቡ በተሰበረበት፣ ዙሪያው ገደል በሆነበት እና ሀገራችን ወደመቃብር ስፍራነት እየተቀየረች ባለችበት በዚህ ወቅት ምርጫ አካሂዶ መልሶ ስልጣኑን በመቆናጠጥ የጥፋት ዘመቻውን አጠናክሮ ለማስቀጠል የቋመጠውን ቁማርተኛ ልብ ይሏል።

## 5. ከኃይማኖት አባቶች ምን ይጠበቃል?

የኢትዮጵያ ህዝብ በኃይማኖተኝነቱ የሚታወቅ ነው። ባለፉት ሦስት ዓመታት በኃይማኖት ተቋማት ላይ የደረሰው ጥፋት ይህ ነው የሚባል አይደለም። በርካቶችም በኃይማኖታቸው ምክንያት ተጎድተዋል። ህይወታቸውንም አጥተዋል። የኃይማኖት ተቋማት ያለ ምእመኖቻቸው ምንም ናቸውና የኃይማኖት አባቶች ይህን ማንነትን መሰረት ያደረገ እና በንፁሀን ላይ ያነጣጠረ የዘር ፍጅት እንዲሁም ድርጊቱን ችላ በማለት ብሎም በመደገፍ እዚህ ደረጃ ያደረሰውን መንግሥት ተባብረው በማውገዝ ከህዝብ ጎን እንዲቆሙ እንጠይቃለን።


E-mail:balderasnorthamerica@gmail.com Tel: 240-838-1745 P.O. Box 43829

### 6. ዳግመኛ አንሳሳት

በለውጡ መጀመሪያ ወቅትም ሆነ ከዚያ በኋላ የተለያዩ አካላት የሽግግር መንግሥት እንዲቋቋም ሀሳብ ሲያቀርቡ ብዙም ጆሮ ሳይሰጣቸው ቆይቷል። አሻግራችኋለው ሲሉን አምነን እጃችንን የሰጠናቸው መሪም ከየት ወዴት እንዳሻገሩን የአደባባይ ምስጢር ነው። የፈሰሰ ውኃ ባይታፈስም ከዚህ በኋላ ስህተታችንን መድገም የለብንም። ስለሆንም ጊዜ ሳናባክን በአፋጣኝ በሁሉም ወገን ተቀባይነት ያለው የባለአደራ መንግሥት እንዲቋቋም እና ሀገራዊ ውይይት እንዲጀመር ከሁሉም አቅጣጫ ግፊት እንዲደረግ ጥሪያችንን እናቀርባለን።

### 7. ከሀገር ውጪ ለምትኖሩ ኢትዮጵያውያን

በህወሀት የተጀመረውና በኦሮሙማው ወራሪ ቡድን የቀጠለውን ወገኖቻችንን በጅምላ የመፍጀት እና ሀገርን የማፍረስ እቅድ በተበታተነ ትግል ከቶም ልናሸንፈው እንደማንችል መገንዘብ ያስፈልጋል። ስለሆነም ይሄን ፅንፈኛና አሸባሪ ቡድን ለመታገል መንገድ ለጀመራችሁና "ምን ማድረግ እንችላለን?" ብላችሁ ሀገርን የመታደግ ውጥን እየወጠናችሁ ላላችሁ አካላት፣ በተለያየ የሙያ ዘርፍ ለተሰማራችሁ ግለሰቦች፣ ቡድኖች እና ድርጅቶች በአንድ ላይ በመሰባሰብ ሀገራችንንና ህዝባችንን ከመከራና ከእልቂት እንድንታደግ ታላቅ የሀገር-አድን ጥሪ እናቀርባለን ::

ይኽን ሀገር ወዳድ ስብስብ መቀላቀል የምትሹ በስልክ ቁጥር **+1 707 955 5466** መደወል ይቻላል። ወይም በኢ-ሜይል አድራሻ **balderaspr@gmail.com** መልዕክት መላክ ይቻላል።

ሀገራችንን ለማዳን ቢረፍድም አልመሸም እና በጋራ እንነሳ!
ፈጣሪ ኢትዮጵያን እና ሕዝቦችዋን ከመከራ ይታደግ!
ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!